8ኛ ዓመት ቁጥር 6
8th Year No. 6

ባህር ዳር ጥር 26/1995 ዓ/ም
Bahir Dar 3rd Day of Feburary, 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ ብር 4.50
Unit price ---------

Contents

አዋጅ ቁጥር 82/1995 ዓ.ም
የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶችን በአዲስ መልክ ማደራጃ አዋጅ

Proclamation No. 82/2003
Reorganizing of Urban and Rural Water Supply and Sewerage Services Proclamation

አዋጅ ቁጥር 82/1995 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶችን በአዲስ መልክ ለማደራጀት የወጣ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልል የከተማና የገጠር መጠጥ ውኃና ፍሳሽ አገልግሎቶች ለኗሪው ሕብረተሰብ ጥራቱን የጠበቀ ንፁህ የመጠጥ ውኃ በበቂ መጠን እና በአስተማማኝ ሁኔታ ለማቅረብ እንዲችሉና እንደ አንድ የመሠረተ ልማት አውታርም ውሃ ለኢንዱስትሪና ከተማ ልማት የሚያበረክተውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በተገቢው ሁኔታ ማግኘት እንዲቻል አደረጃጀታቸውን መርምሮ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በንፁህ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ተጠቃሚውን ሕብረተሰብ በቀጥታ በማሣተፍ የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ የውሃ ሃብት አስተዳደር ፖሊሲ መሰረት የከተሞችን መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች የኢንቨስትመንት፣ አሬሽንና ጥገና ወጪያቸውን የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች ደግሞ የኦፕሬሽንና ጥገና ወጪያቸውን በሚያስመልስ መልኩ የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

Proclamation No. 82/2003

A Proclamation to Provide for the Recognizing of the Amhara National Region Urban and Rural Water Supply and Sewerage Services

WHEREAS, it has become necessary to examine and improve the organization of the Amhara National Region water supply and sewerage services in order to enable them supply the public with potable and reliable amount of water; and as it is one feature of infrastructure, to properly make it accessible for its exceptional contribution to the industrial and urban development;

WHEREAS, it has become necessary, through direct participation of the public to cause the water supply and sewerage services provide expeditious services;

WHEREAS, it is deed appropriate, pursuant to the Ethiopian water Resource Management Policy, to set conditions in such a way that the investment, operation and maintenance of urban water supply and sewerage services and the operation and maintenance of Rural Water supply and sewerage services bring about the recovery of their costs;

በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶችን እንደገና ለማደራጀት የወጣ አዋጅ ቁጥር 82/1995 ዓ/ም'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ቦርድ'' ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሰረት የተቋቋመ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ጽ/ቤት የበላይ አመራር አካል ነው።
2. "ጽህፈት ቤት'' ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 እና 18 ድንጋጌዎች ሥር የተገለፀት የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ጽ/ቤቶች ናቸው ።
3. "ቢሮ'' ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ውሃና ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ነው።
4. "የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያ'' ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ውጭ ያሉትንና በገጠር የውሃ ግንባታ ተሰርቶላቸው አገልግሎት የሚሰጡትን የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎች የሚገልጽ ነው።
5. "የውሃ ኮሚቴ'' ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 የተገለፀውን የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያን የሚመራ የበላይ አካል ነው።

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው በአማራ ብሔራዊ ክልል የከተማና የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች ላይ ብቻ ይሆናል።

NOW, THEREFORE, according Article 49 sub-Article 3(1) of the 2001-Revised constitution of the Amhara National Region, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Reorganizing of Urban and Rural Water supply and Sewerage Services Proclamation No. 82/2003."

2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1. "Board" means the highest management organ of the water supply and sewerage services office established in accordance with Article 6 of this Proclamation.
2. "Office" means the water supply and sewerage offices indicated under provisions of Article 5 and 18 of this Proclamation.
3. "Bureau" means Water and Mineral Resources Bureau of the Amhara National Region.
4. "Rural Water Supply Sewerage Station" means the rural water supply and sewerage stations constructed and providing services in rural areas separate from those indicated under Article 4 of this proclamation.
5. "Water Committee" means the highest organ that directs the Rural Water Supply Station indicated under Article 26 of this Proclamation.

3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable only to the Amhara National Region Urban and Rural water supply and sewerage services.

3. የከተሞችን የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ደረጃዎች ለመወሰን የሚያስችል ዝርዝር መስፈርት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

4. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰኑ መስፈርቶችን መነሻ በማድረግ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶችን ደረጃ በየጊዜው ሊያሻሽል ይችላል።

5. ቢሮው በራሱ አነሳሽነት የገጠር መጠጥ ውኃና ጣቢያዎችን ወደ ከተማ መጠጥ ውኃና ፍሳሽ አገልግሎቶች ደረጃ ሊያሳድግ ይችላል።

6. ቢሮው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ቁጥር ሀ እስከ ፊደል ተራ ቁጥር ረ ለተዘረዘሩት የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ደረጃዎች የሚመጥን መዋቅር አዘጋጅቶ ለመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች በመመሪያ ያስተላልፋል።

6. አደረጃጀት

ከዚህ በላይ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ ሀ እስከ ሠ የተመለከቱት የከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች አደረጃጀት እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ. የሥራ አመራር ቦርድ፣

ለ. ጽህፈት ቤት፣

ሐ. ሌሎች አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች።

7. ቦርድ ስለማቋቋም

1/ ቦርድ የሚቋቋመው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ስር ከፊደል ተራ ቁጥር ሀ እስከ ሠ ድረስ የተመለከቱት ደረጃዎች ባላቸው አገልግሎቶች ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቋቋመው የሥራ አመራር ቦርድ አባላትና ቁጥር ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

3. Criteria for Urban Water Supply and Sewerage Services standards shall be determined by regulation to be issued for the implementation of this proclamation.

4. The Bureau, on the basis of the criteria determined by regulation to be issued pursuant to sub-Article 3 of this Article, shall periodically improve the standard of water supply and sewerage services.

5. The Bureau may, up on its self-initiations, upgrade rural water supply and sewerage services up to the standards of urban water supply and sewerage services.

6. The Bureau shall prepare a structure to specify water supply and sewerage services standards for those mentioned from 'a' to 'f' of sub-Article 1of this Article and transfer same by regulation to the Water Supply and Sewerage Services thereof.

6. Organization

The organization of Urban Water Supply and Sewerage Services indicated under Article 5 sub-Article 1 'a' to 'f' shall be as follows:

a. Management Board,

b. Office,

c. Other necessary departments.

7. Establishment of Board

1. Board shall be established for the services with standards indicated under Sub-Article 1 'a' to 'f' of Article 5 of this proclamation.

2. The members and number of the management Board to be established according to sub-Article 1 of this Article shall be determined by regulation to be issued for the implementation of this proclamation.

3. የቦርዱ ተጠሪነት የከተማ ምክር ቤት በተቋቋመበት ከተማ ለዚሁ ምክር ቤት፣ ይህ ምክር ቤት ባልተቋቋመባቸው ሥፍራዎች ደግሞ እንደሁኔታው ከተማው ለታቀፈበት ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል::

4/ የቦርዱ ሰብሣቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ቦርዱ ተጠሪ በሆነለት አካል ውሣኔ ካባላቱ መካከል ተመርጦ ይሰየማል::

8. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ጽ/ቤቱን ያደራጃል፣ በበላይነት ይመራል፣

2. የጽህፈት ቤቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የሥራ ዕቅድ እና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ መርምሮ ያፀድቃል፣ ተግባራዊ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ሥራውን በየጊዜው ይገመግማል፣

3. ለአዳዲስ የግንባታ ሥራዎች የሚያስፈልገውን የኢንቨስትመንት በጀት በተመለከተ ቦርዱ ተጠሪ ለሆነለት አካል አቅርቦ ያስፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፣

4. የንፁህ ውሃ ተጠቃሚውን ሕብረተሰብ በማወያየት የተሻለ እና ቀልጣፋ አሠራር ተቀርጾ በጽ/ቤቱ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

5. የተጠናከረ የፋይናንስ እና የንብረት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ በሚቀርብለት የኦዲት ሪፖርት ላይ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል፣

6. የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ የአገልግሎት ኃላፊውን አወዳድሮ ይመድባል፣ አምነት ሲያጣበትም ከሥራ ያሰናብታል፣

7. ለመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቱ ጥንካሬና አድገት የሚያግዙ የተለያዩ የገንዘብና የቁሳቁስ ምንጮች ያፈላልጋል፣

8. ልዩ ልዩ የአበልና ጥቅማ ጥቅም ጥያቄዎችን እየመረመረ ውሣኔ ይሠጣል፣

3. The accountability of the Board, wherein a city council is established, shall be to this council; and in places wherein this council is not established, its accountability shall be to the council of the Wareda Administration in which the town is embraced accordingly.

4. The Chairperson of the Board shall be elected in accordance with sub-Article 3 of this Article from among the members by decision of the organ to which the Board is accountable.

8. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers and duties:

1. Organize the Office and direct its overall activities;

2. Examine and approve short, medium and long-term work plan and the executionary budget of the office, follow up and control its practical implementation, evaluate periodically its performances;

3. Submit and have it approved the investment budget necessary for new constructions to the organ to which the Board is accountable, follow up and control its implementation;

4. Discuss with customers of potable water to bring about the formulation of a better and expeditious process and cause it implemented by the office;

5. Put in place a consolidated system of finance and property control, follow up its implementation and pass appropriate decisions on audit report submitted to it;

6. Assign Head of the Water Supply and Sewerage Services in competition and discharge him for loss of confidence;

7. Search for various financial and material resources for the consolidation and promotion of water supply and sewerage services;

8. Examine and decide over requests of various allowance and benefits;

9. የመጠጥ ውሃ ታሪፍ በጽ/ቤቱ ተጠንቶ ሲቀርብለት መርምሮ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተጠሪ ለሆነለት አካል ለውሣኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ለጽ/ቤቱ በማሣወቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

10. የሥራ እንቅስቃሴውን በሚመለከት ተጠሪ ለሆነለት አካል በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል።

9. Examine a reviewed water tariff submitted to it by the office, and forward same for decision to the organ of its accountability in accordance with sub-Article 3 of Article 7, and upon approval follow up its practical implementation having made prior cognizance to the office;

10. Submit performance report periodically to the organ of its accountability.

9. ስለ ቦርዱ ስብሰባ

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንዳስፈላጊነቱ የሚጠሩ አስቸኳይ ስብሰባዎችን የሚያግድ አይሆንም።

3. ከቦርዱ አባላት መካከል ሁለት ሶስተኛው በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

4. የቦርዱ ውሣኔዎች በተሰብሳቢዎች አብላጫ ድምፅ ይተላለፋሉ። የተሰጠው ድምፅ እኩል ለእኩል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ሰብሣቢው የደገፈው ወገን የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል።

9. Board Meetings

1. The Board shall have a regular meeting once every month.

2. The Provisions under sub-article 1 of this Article shall not prohibit convening extra ordinary meetings, as deemed necessary.

3. There shall be a quorum when two-thirds of members of the Board present at a meeting.

4. Decisions of the Board shall be passed by majority vote of the assembly. Where the vote draws in a tie, the motion supported by the chairperson shall be the decision of the Board.

10. ስለ ውኃና ፍሳሽ አገልግሎቶች ጽ/ቤት

እያንዳንዱ የከተማ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሰረት የእለት ከእለት ሥራዎችን የሚያከናውንበት የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል።

10. Water Supply and Sewerage Services Office

Every Urban Water Supply and Sewerage Service shall, in accordance with this proclamation, have its own office to undertake its every day tasks.

11. ስለ ጽህፈት ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

ጽ/ቤቱ ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. አገልግሎቱ ለተቋቋመበት ከተማ ነዋሪ ሕዝብ ንጽህናውንና ጥራቱን የጠበቀ ውሃ በበቂ መጠን ያቀርባል፣

2. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመቀናጀት አቅም በፈቀደ መጠን የፍሳሽ አወጋገድ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አገልግሎት ይሰጣል፣

3. የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ለሚጠይቁ ተጠቃሚ ግለሰቦች እና ድርጅቶች እንደጥያቄው ቅደም ተከተል የውሃ መስመሮችን ያስገባል፣ ሲበላሹም ይጠግናል፣

11. Duties and Responsibilities of the Office

The office shall have the following duties and responsibilities:

1. Provide adequate, clean and good quality water for town dwellers to whom the service is established;

2. Put in place, as much as possible, sewer disposal system being integrated with relevant bodies, and render service thereby;

3. Lay water pipes to individuals and organizations that require potable water service in the order of their requests, and repair pipes when damaged;

4. በሥራ ላይ ባለው ታሪፍ መሠረት ከመጠጥ ውሃና ፍሣሽ እንዲሁም ከሌሎች የተለያዩ አገልግሎቶች የሚገኙትን ገቢዎች በሚገባ ይሰበስባል።

5. በተዘረጋለት ሥርዓት መሠረት የአገልግሎቱ ፋይናንስና ንብረት በሚገባ መያዙንና ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፤

6. ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ተፈላጊ መሣሪያዎችን እና ሌሎች መገልገያዎችን ይገዛል፤

7. በቦርዱ የቅድሚያ እውቅናና ፈቃድ ማናቸውንም እርዳታ፣ ስጦታና ብድር በአገልግሎቱ ስም ይቀበላል፣ ይዋዋላል፤

8. አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ በቦርዱ ሲፈቀድም ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

9. ስለ መጠጥ ውሃ ምርትም ሆነ በሥሩ ስለተተከሉ መሣሪያዎች አጠቃቀምና አያያዝ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፣ ይጠብቃል፣ በየወቅቱም ለቢሮው ያስተላልፋል፤

10. ለመጠጥ ውሃ ሥርጭት አገልግሎት የተተከሉ የውኃ መሣቢያ መሣሪያዎችም ሆኑ ሌሎች ተመሣሣይ መገልገያዎች ተበላሽተው የመጠጥ ውሃው አገልግሎት እንዳይቋረጥ መጠባበቂያ መሣሪያዎች እንዲኖሩት ያደርጋል ፣ ሲበላሹ በራሱ ወጭ ያስጠግናል፤

11. የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ማሻሻያ ወይም ማስፋፊያ ሥራ መስራት ሲያስፈልገው በቢሮው በሚዘጋጀው ስታንዳርድ ዲዛይን መሠረት በማዘጋጀት ለቦርዱ አሣውቆ ተግባራዊ ያደርጋል፣

12. ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን በማጥናት ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፤

13. በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ውል ይዋዋላል የንብረት ባለቤት ይሆናል፤

14. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ይፈፅማል።

4. Collect properly revenues, in accordance with the tariff in effect, from water supply and sewerage as well as other various services;

5. Ensure, according to the system put in place, the proper management and implementation of finance and property of the service for the objective targated;

6. Purchase necessary tools and other utilities under instruction rendered to it by the Board;

7. Receive any donations, gifts and loans as well as enter into contracts in the name of the service with prior cognizance and authorization of the Board;

8. Devise new methods of operation and implement them upon approval by the Board;

9. Record and keep essential items of information as to water production, utilization and maintenance of tools installed under its control, and transfer same regularly to the Bureau;

10. Keep reserve tools so as water distribution may not be interrupted due to failures of water pumps or other similar apparatuses; and when damaged make them repaired on its own expense;

11. Effectuate water supply service improvements or extension activities, when it deems necessary, according to the standard design prepared by the Bureau with prior confirmation to the Board;

12. Submit the analysis of various benefits to the Board for approval;

13. Sue, be sued, enter into contracts and own property in its own name;

14. Carry out other duties that help it achieve its objectives.

12. ስለ ጽ/ቤቱ ኃላፊ

የጽ/ቤት ኃላፊው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በዚህ አዋጅ እና ከቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ጽ/ቤቱን በኃላፊነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣
2. ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል::
3. የጽህፈት ቤቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የሥራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
4. ለውሣኔ አሰጣጥ የሚረዱ መረጃዎችን አዘጋጅቶ ለቦርዱ ይሰጣል፣ በየሶስት ወሩም የሥራ ዘገባ አያዘጋጀ ያቀርባል፣
5. በጽህፈት ቤቱ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሣል፣
6. ጽ/ቤቱን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፣
7. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

13. የበጀት ምንጭ

የጽ/ቤቱ በጀት ከሚከተሉት የሚመነጭ ይሆናል:-

1. ከውሃ ሽያጭ የሚሰበሰብ ገቢ፣
2. ከተለያዩ አገልግሎቶች አሰጣጥ የሚመነጭ ክፍያ፣
3. ከአገልግሎቱ ልዩ ልዩ ንብረቶች ሽያጭ የሚገኝ ገቢ፣
4. ከተለያዩ ምንጮች የሚገኝ የአይነትና የጥሬ ገንዘብ እርዳታ እና ብድር፣
5. ህብረተሰቡ ለመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቱ መስፋፋት ከሚያደርገው መዋጮ::

12. The Head of the Office

The Head of the Office shall have the following powers and duties:

1. Direct and supervise the Office in accordance with this Proclamation and instruction entrusted to him by the Board;
2. Recruit, administer and discharge employees;
3. Prepare and submit short, medium and long term work plan and budget of the office to the Board and execute same upon approval;
4. Prepare and submit supporting documents for decision making to the Board and quarterly performance report thereto;
5. Open and manage bank account in the name of the office;
6. Represent the office in all its relations with third parties;
7. Discharge other duties entrusted to him by the Board.

13. Budget Sources

The budget of the office shall be drawn from the following sources;

1. Revenues collected from the sales of water;
2. Earnings generating from various service rendering activities;
3. Revenue obtained from the sales of various properties of the service;
4. Donations and loans in cash and in kind from various sources;
5. Public contributions intended for the expansion of water supply and sewerage service;

14. ስለ ገቢ አጠቃቀምና የገንዘብ አስተዳደር ስርዓት

1. ጽህፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሰረት የሚሰበሰበውን ገቢ ለታቀደለት አላማ የሚውል ግዴታ አለበት።

2. ጽ/ቤቱ ቢሮው በሚያዘጋጃቸው የፋይናንስና የግዥ ማንዋሎች መሠረት ሥራውን ያከናውናል።

3. የጽ/ቤቱ ሂሣብ በየጊዜው በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚወክለው አካል ይመረመራል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ እርሱ በሚሰይመው አካል የጽ/ቤቱ ሂሣብ እንዲመረመርና ውጤቱ እንዲቀርብለት ሊያደርግ ይችላል።

15. ስለ ንብረት አስተዳደር

እያንዳንዱ የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎት ለውሃ አቅርቦት የተሠሩ ግንባታዎችን፣ በየሥፍራው የተተከሉ የውሃ ማጠራቀሚያ እና ማስተላለፊያ መሣሪያዎችን እና ሌሎች መሰል መገልገያዎችን ተረክቦ የንብረቱ ባለቤት በመሆን በአግባቡ የመጠቀም፣ የማስተዳደርና ደህንነታቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት።

16. ስለ ሰው ሀይል አስተዳደር

በቦርድ የሚተዳደሩ የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች የሰው ኃይል አስተዳደር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/85 ዓ.ም መሠረት ይሆናል።

ክፍል ሶስት

የወረዳ የውሃ ዴስክ ስለሚያስተዳድራቸው የንዑስ ከተማ መጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቶች

17. ስለ አገልግሎቶቹ አይነት

14. Revenue Utilization and Finance Administration System

1. The Office shall, in accordance with Article 13 of this proclamation, have an obligation to implement the revenue for the objectives intended.

2. The Office shall discharge its duties according to the finance and purchasing manuals prepared by the Bureau.

3. The accounts of the office shall be periodically audited by the Auditor-General of the Region or by a body it designates.

4. Notwithstanding to the provision of sub-Article 3 of this Article, the Board may, whenever it gets necessary, cause the accounts of the office be audited at any time and have a report by a body it designates.

15. Property Administration

Each water supply and sewerage services shall be responsible to take over, utilize properly, administer and safeguard water supply constructions, water reservoirs, transmission lines and other similar utilities.

16. Personnel Administration

The administration of personnel under the Board of Water Supply and Sewerage Services shall be in accordance with labour proclamation No. 42/1993.

PART THREE

Small Towns Water Supply and Sewerage Services Administered by the Woreda Water Desk

17. Type of Services

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 1 በፊደል ተራ ቁጥር ረ የተመለከቱት የንዑስ ከተማ መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች የሚተዳደሩት በወረዳ የውሃ ዴስክ ክትትልና ጥበቃ ስር ይሆናል።

18. አደረጃጀት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 ስር የተመለከቱት ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቶች የሚከተለው አደረጃጀት ይኖራቸዋል፦

ሀ/ የሥራ አመራር ድጋፍ ሠጪ ኮሚቴ፣

ለ/ የአገልግሎቱ ጽ/ቤት፣

ሐ/ የአገልግሎቱ ኃላፊና ሌሎች የሥራ ክፍሎች።

19. ስለ ወረዳ የውኃ ዴስኩ ሥልጣንና ተግባር

የእያንዳንዱ የወረዳ የውሃ ዴስክ ቢሮው በተቋቋመበት አዋጅ የተሰጠው ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

ሀ/ ጽህፈት ቤቱን ያደራጃል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣

ለ/ የጽ/ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና ማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅን ይመረምራል፣ ያፀድቃል፣

ሐ/ ጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባሩን በሚገባ ተጠቅሞ ግዴታውን መወጣቱን ይከታተላል፣

መ/ የጽህፈት ቤቱን የሥራ ሪፖርት በየጊዜው ይገመግማል፣

ሠ/ በሚቀርብለት የኦዲት ሪፖርት መሠረት አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል፣

ረ/ የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቱ ቢሮው በሚያዘጋጀው የአስተዳደር፣ የፋይናንስና የግዥ ማንዋል መሠረት ሥራውን ማከናወኑን በበላይነት ይቆጣጠራል፣ያስፈጽማል፣

ሰ/ የጽ/ቤቱን ኃላፊ አወዳድሮ ይመድባል።

Water Supply and Sewerage Services of small towns indicated in Article 5 sub-Article 1(a) to (f) shall be under the supervision and control of the Woreda Water Desk.

18. Structure

The Water Supply and Sewerage Services under Article 17 of this proclamation shall have the following structure:

a. Supporting Management committee;

b. Office of the Service;

c. Head of the Office and other departments.

19. Powers and Duties of the Woreda Water Desk

Without Prejudice to the responsibilities provided for by the proclamation by which the Bureau is established, each Woreda Water Desk shall have the following specific duties and responsibilities:

a. Organize and supervise the activities of the Office;

b. Examine and approve the annual work plan and executionary draft budget of the office;

c. Follow up that the Office has discharged its responsibility by properly exercising its powers and duties;

d. Evaluate periodically the performance report of the office;

e. Give necessary decision according to audit report submitted to it;

f. Supervise and execute that the water supply and sewerage services discharges its duties according to the Administration, Finance and Purchase manual prepared by the Bureau;

g. Assign the Head of the Office in competition.

20. ስለ ጽ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

ጽ/ቤቱ ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

1. አገልግሎቱ ለተቋቋመበት ከተማ ነዋሪ ሕዝብ ንጽህናውንና ጥራቱን የጠበቀ የመጠጥ ውሃ በበቂ መጠን ያቀርባል፤
2. የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ለሚጠይቁ ተጠቃሚ ግለሰቦች እና ድርጅቶች እንደጥያቄያቸው ቅደም ተከተል የውሃ መስመሮችን ያስገባል፣ ሲበላሹም ይጠግናል፤
3. በሥራ ላይ ባለው ታሪፍ መሠረት ከመጠጥ ውሃና ፍሳሽ እንዲሁም ከሌሎች የተለያዩ አገልግሎቶች የሚገኙትን ገቢዎች በሚገባ ይሰበስባል፤
4. የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎቱን ያስተዳድራል፤
5. አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ በውሃ ዴስክ ሲፈቀድም ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
6. ስለ መጠጥ ውሃ ምርትም ሆነ ስለመሣሪያዎች አጠቃቀም የሚያስፈልጉ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፣ ይጠብቃል፤
7. ስለ መጠጥ ውሃ ምርትም ሆነ በሥሩ ስለተተከሉ መሣሪያዎች አጠቃቀምና አያያዝ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በየወቅቱ ለቢሮው ያስተላልፋል፤
8. ለመጠጥ ውኃ ሥርጭት አገልግሎት የተተከሉ የውኃ መሣቢያ መሣሪያዎችም ሆኑ ሌሎች ተመሣሣይ መገልገያዎች ተበላሽተው የውኃው አገልግሎት እንዳይቋረጥ መጠባበቂያ መሣሪያዎች እንዲኖሩት ያደርጋል ፣ ሲበላሹ በራሱ ወጭ ያስጠግናል፤
9. የመጠጥ ውሃ አገልግሎት ማሻሻያ ወይም ማስፋፊያ ሥራ መስራት ሲያስፈልገው ለዚሁ የሚገባውን ዲዛይን ለወረዳው የውሃ ዴስክ አቅርቦ ያስፀድቃል፤ ሲፈቀድለትም በሥራ ላይ ያውላል፤

20. Duties and Responsibilities of the Office

The Office shall have the following duties and responsibilities:

1. Supply safe and adequate potable water for town dwellers to whom the service is established;
2. Lay water pipes to individuals and organizations that require potable water service in the order of their requests, and repair pipes when damaged;
3. Collect properly revenues from water supply and sewerage and other services in accordance with the tariff in effect;
4. Administer the water supply and sewerage services;
5. Devise new methods of operation and execute same upon approval of the water Desk;
6. Keep records and maintain information necessary for water harvest and utilization of instruments;
7. Pass frequently information to the Bureau on water harvest and utilization as well as maintenance of tools installed under its control;
8. Cause to have reserve implements in order to prevent disruption of potable water distribution due to the damage of water pumps and other similar apparatuses; and make them repaired on its own expenses when damaged;
9. Submit appropriate design to the Woreda water Desk and have it approved, as may be necessary, to improve water services or carry out expansion activities, and thereby execute same;

10. በሥራ ላይ ያለውን ታሪፍ አሰራነት እያጠና ውጤቱን ከውሳኔ ሃሳብ ጋር በውሃ ዴስኩ አማካኝነት ለሥራ አመራር ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ያቀርባል፣

11. የፋይናንስ አጠቃቀምንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ለሥራ አመራር ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ በተጠየቀበት ጊዜ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፣

12. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ይፈፅማል::

21. ስለጽ/ቤቱ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

የንዑስ ከተማ መጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ኃላፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

1. በዚህ አዋጅና ከወረዳ ውሃ ዴስኩ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ጽ/ቤቱን በኃላፊነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

2. ቢሮው በሚያወጣው የሠው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የጽ/ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

3. የጽ/ቤቱን አመታዊ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት ተጠሪ ለሆነለት አካል ያቀርባል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

4. ለውሣኔ አሠጣጥ የሚረዱ መረጃዎችን ለውሃ ዴስኩ ይሠጣል፣በየሶስት ወሩም የሥራ ዘገባ እያዘጋጀ ያቀርባል፣

5. በጽ/ቤቱ ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሣቅሣል::

6. ጽ/ቤቱ በሚከሰስበትም ሆነ በሚከሰስበት ጊዜ ጽ/ቤቱን የመወከል ኃላፊነት ይኖረዋል፣

7. ከሥራ አመራር ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ጋር በየጊዜው በመገናኘትና የተሻሻሉ አሠራሮችን በመቀበል ለውሃ ዴስኩ እያቀረበ ተግባራዊ ያደርጋል::

10. Review and submit the feasibility of the tariff in effect together with recommendations to the Management Supporting Committee through the Water Desk;

11. Have responsibility to submit financial utilization and other important documents to the Management supporting committee whenever requested;

12. Discharge other functions that facilitate the execution of its objectives.

21. Duties and Responsibilities of the Head of the Office

Head of water supply and sewerage services of small towns shall have the following duties and responsibilities.

1. Direct and supervise the office according to this proclamation and directives given by the woreda water Desk;

2. Recruit, administer and discharge employees of the Office according to the Personnel Administration directives to be issued by the Bureau;

3. Submit annual work plan and budget of the office to the organ to which it is responsible, and execute same upon approval;

4. Provide information helpful to decision-making to the Water Desk, and submit a performance report in every three months;

5. Open and manage bank account in the mane of the office;

6. Have responsibility to represent the Office when it sues or be sued;

7. Meet regularly with the Management supporting committee and introduce improved operations and submit them to the Water Desk, and effectuate thereto;

22. የሥራ አመራር ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. ለመጠጥ ውሃና ፍሣሽ አገልግሎቱ የሥራ አመራር ድጋፍ የሚሰጥና በመጠጥ ውሃ አገልግሎቱ ተጠቃሚ ህብረተሰብ የሚመረጥ "የሥራ አመራር ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ" ይቋቋማል።

2. በኮሚቴው ውስጥ የሴቶች ተሣትፎ አስገዳጅ ይሆናል።

23. የሥራ አመራር ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የሥራ አመራር ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

1. በህብረተሰብ ተሣትፎ የሚከናወኑ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

2. የውሃ ጣቢያዎችን ለማስፋፋት፣ ለማሻሻልና ከጽ/ቤቱ አቅም በላይ የሆኑ ወጪዎችን በህብረተሰቡ እንዲሸፈኑ ይቀሰቅሣል፣ ያስተባብራል፤

3. የሚገነቡ የውሃ ጣቢያ አውታሮች ከተጠቃሚው ህብረተሰብ ፍላጐት ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን እየተከታተለ ለጽ/ቤቱ አስፈላጊውን የምክር አገዛ ያደርጋል፤

4. በህብረተሰቡና በሌሎች ለጋሽ አካሎች የተገኘው እርዳታ በአግባቡ ለታቀደለት አላማ መዋሉን ይከታተላል፣ይገመግማል፤

5. ሌሎች ተጠቃሚው ህብረተሰብ የተስማማባቸውን አዳዲስ እና የተሻሻሉ አሠራሮች በጽ/ቤቱ በኩል ተግባራዊ እንዲደረጉ ጥረት ያደርጋል።

24. የበጀት ምንጭ

የጽ/ቤቱ የበጀት ምንጮች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ሥር የተመለከቱት ይሆናሉ።

22. Establishment of Management Supporting Committee

1. "Management Supporting Committee" elected by the water supply service customers shall be established to provide support to the water supply and sewerage service management.

2. Participation of Women in the committee shall be obligatory.

23. Duties and Responsibilities of Management Supporting Committee

The Management Supporting Committee shall have the following duties and responsibilities:

1. Coordinate activities run by public participation;

2. Initiate and coordinate the community to cover costs, which are beyond the capacity of the Office, in order to expand and improve water stations;

3. Follow up that the construction of water infrastructures is conformable with the interest of the customers and provide necessary advice to the office;

4. Follow up and evaluate that the donations secured from the community and other donors are properly utilized for objectives intended;

5. Put an effort to execute through the Office other new and improved methods of operation on which the community agrees.

24. Budget Sources

Budget Sources of the Office shall be those indicated under Article 13 of this Proclamation.

25. ስለ በጀትና የፋይናንስ አስተዳደር

ጽ/ቤቱ የሚሰበስበው ገቢ አጠቃቀምና የሠው ኃይል አስተዳደር ቢሮው በሚያዘጋጃቸው መመሪያዎች መሰረት የሚፈፀም ይሆናል።

ክፍል አራት

ስለገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎች ምስረታ፣ አደረጃጀትና ኃላፊነት

26. ስለገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎችና ኮሚቴዎች መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ በተለያዩ የገጠር አካባቢዎች የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎች እና የውሃ ኮሚቴዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ይቋቋማሉ።

2. የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያ የሚመራው በውሃ ኮሚቴ ሲሆን ኮሚቴው አካባቢው በሚታቀፍበት ወረዳ ውሃ ዴስክ እና በአስተዳደር አካላት አስተባባሪነት የጋራ ትብብር እና በተገልጋዩ ህዝብ ምርጫ የሚቋቋም ይሆናል።

27. ስለ ውሃ ኮሚቴ አወቃቀርና ስብጥር

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎችን በበላይነት የሚመራና ከ 5 እስከ 7 አባላት የሚካተቱበት የውሃ ኮሚቴ ይቋቋማል።

2. የኮሚቴው አባላት ተዋፅኦ ተገልጋዩ ሕብረተሰብ የሚመርጣቸው የውሃ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ ከአትም በላይ ካልሆነ በስተቀር ከኮሚቴው አባላት አብዛ ኛቹ ሴቶች መሆን ይገባቸዋል።

3. የኮሚቴው አባላት የአገልግሎት ዘመን ሶስት አመት ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ለተጨማሪ የአገልግሎት ዘመን በድጋሚ ከመመረጥ በዚህ ድንጋጌ አይታገዱም።

28. ስለኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

25. Budget and Finance Administration

Utilization of revenues collected by the office and manpower administration shall be according to the directives prepared by the Bureau.

PART FOUR

Establishment, structure and Responsibility of Rural Water Supply and Sewerage Stations

26. Establishment of water supply and sewerage stations and committees

1. Rural water supply and sewerage stations as well as committees shall be established in various areas of the Region Pursuant to this Proclamation.

2. Rural water supply and sewerage station shall be directed by water committee; the Committee shall be elected through joint coordination of the Worda water Desk and Administrative Organs wherein the station is located and by the election of the community.

27. Structure and Composition of the Water Committee

1. Water committee comprising 5 to 7 members shall, in accordance with this proclamation, be established to direct the activities of water supply and sewerage services stations.

2. The Committee shall compose members elected by the community from among the customers, unless otherwise it is beyond capacity the members of the committee shall mostly be women.

3. Term of service of committee members shall be three years; however, as the case may be, the re-election of them for another term of service is not prohibited by this provision.

28. Duties and Responsibilities of the Committee

Rural Water Supply and Sewerage Committee shall, in accordance with this Proclamation, have the following duties and responsibilities:

ሀ/ የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያን የእለት ከእለት ሥራ የሚያከናውኑ ሠራተኞችን በስምምነት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣ ያሰናብታል፣

ለ/ የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎችን ተገልጋዩ ህብረተሰብ በራሱ ተሣትፎ እንዲጠብቃቸው እና እንዲንከባከባቸው ያደርጋል፣

ሐ/ በሥሩ የሚገኘውን የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያ ለማስተዳደር እና ለመጠገን የሚያስፈልገውን ወጭ ለመሸፈን ከተጠቃሚው ሕብረተሰብ የሚፈለገውን የውሃ ታሪፍ በየጊዜው እያጠና ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ በማቅረብ ያስወስናል፣ ያስፈፅማል፣

መ/ በሥሩ ያሉ የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያ ሠራተኞች እና የተጠቃሚው ሕብረተሰብ ተወካዮች ከየደረጃው አስተዳደርና ከሚመለከተው የወረዳ የውሃ ዴስክ ጋር በመመካከር የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎች አመራር መሰረታዊ ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል።

29. ስለ ተጠሪነትና የስብሰባ ጊዜ

1. የመጠጥ ውሃና ፍሣሽ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለመረጠው ሕዝብና ላለበት ቀበሌ /ወረዳ አስተዳደር/ ሲሆን በቴክኒክ ረገድ ደግሞ በአቅራቢያው ከሚገኘው የወረዳ የውሃ ዴስክ ጋር በመመካከር ይሆናል።

2. ኮሚቴው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። ሆኖም በዚህ ድንጋጌ ምክንያት ልዩ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን እንደአስፈላጊነቱ ከመጥራት አይታገድም።

30. የበጀት ምንጭ

የገጠር መጠጥ ውኃና ፍሣሽ ጣቢያ በጀት ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ. ከውሃ ሽያጭ የሚሰበሰብ ገቢ፣

ለ. ከተለያዩ የቴክኒክ አገልግሎቶች የሚሰበሰብ ክፍያ፣

ሐ. ከንብረት ሽያጭ የሚገኝ ገቢ ፣

a. Recruit on agreements, administer, control and discharge employees who carryout daily activities of Rural water supply and sewerage station;

b. Cause the community, being served, to safeguard and look after Rural water stations;

c. Review the tariff required of the community necessary to cover the administering and repairing costs of the Rural Water Supply and Sewerage Stations under its control; submit same to customers, have it approved and cause for its implementation;

d. Cause the Water Supply and Sewerage Station Management take basic trainings in consultation with the employees of Rural water supply and sewerage services stations under its control, representatives of the customer community, administration organs at all levels and relevant Woreda water Desk.

29. Accountability and Meetings

1. Water Supply and Sewerage Committee shall be responsible to the electorate and to the kebele whenever it is located /Woreda Administration/; and it shall be in touch with its Woreda water Desk regarding technical matters.

2. The Committee shall hold a regular meeting once every month; however, it is not prohibited to convene special and extra ordinary meetings, as deemed necessary, due to this provision.

30. Budget Sources

Budget sources of Rural Water Supply and Sewerage Station shall be the following:

a. Revenue collected from water sales;

b. Fee collected from various technical services;

c. Revenue obtained from property sales;

መ. ከግለሰቦችና ከድርጅቶች የሚገኝ ስጦታና እርዳታ፣

ሠ. ከውሃ ተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ መዋጮ::

31. የሂሳብ መዛግብት

1. የውሃ ኮሚቴ ትክክለኛ እና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል::

2. የኮሚቴው የገንዘብ አስተዳደር ቢሮው አዋጁን መሠረት አድርጐ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈፀማል::

3. የኮሚቴው ሂሳብ የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያው፣ የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤትና የታቀፈበት የወረዳ ውሃ ዴስክ ተመካክረው በሚሰይሙት አጣሪ አካል በማናቸውም ጊዜ ይመረመራል::

32. ስለንብረት አስተዳደር

የገጠር መጠጥ ውሃና ፍሣሽ ጣቢያዎች የንብረት አስተዳደር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል::

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

33. የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የከተማና የገጠር መጠጥ ውኃና ፍሣሽ አገልግሎቶች በባለቤትነት ያፈሯቸው ንብረቶች፣ ያገኟቸው የባለቤትነት መብቶች፣ የገቧቸው አዳዎችና ሌሎች ግዴታዎች በሙሉ በዚህ አዋጅ ለተቋቋሙትና እንደገና ለተደራጁት የከተማና የገጠር መጠጥ ውኃና ፍሳሽ አገልግሎቶች ተላልፈዋል::

34. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችን የማውጣት ሥልጣን አለው::

35. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን አለው::

d. Gifts and donations obtained from individuals and institutions;

e. Contributions collected from customers.

31. Books of Accounts

1. The Water Committee shall keep complete and accurate books of accounts.

2. Finance Administration of the Committee shall be implemented according to the directives to be issued by the Bureau, pursuant to this proclamation.

3. Accounts of the Committee shall be audited at any time by an inquiry body designated through discussions held between the Rural Water supply and Sewerage Station, Woreda Administration Council and Water Desk wherein the Station is located.

32. Property Administration

Property Administration of Rural Water Supply and Sewerage Stations shall be executed in accordance with provisions under Article 15 of this Proclamation.

PART FIVE

Miscellaneous Provisions

33. Transfer of Rights and Duties

All Properties, Ownership rights, debts and other liabilities of Urban and Rural Water Supply and Sewerage services prior to this Proclamation are hereby transferred to the reorganized Urban and Rural Water Supply and Sewerage Services.

34. Powers to Issue Regulations

The Council of the Regional Governmental shall have the power to issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

35. Powers to Issue Directives

The Bureau shall have the power to issue directives necessary for the implementation of this Proclamation.

36 ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጐች

1. የከተማና የገጠር መጠጥ ውኃና ፍሳሽ አገልግሎቶችን በአዲስ መልክ ለማደራጀት የወጣው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 19/1993 ዓ/ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

37. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር 26 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ጥር 26 ቀን 1995 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

36. Inapplicable Laws

1. Reorganizing of Urban and Rural Water Supply and Sewerage Services Executive Committee Regulation No. 19/2001 is hereby repealed.

2. Any Law, regulation, directive or practice inconsistent with this Proclamation shall not be applicable on matters provided in this Proclamation.

37. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of the 3rd day of February, 2003.

Done at Bahir Dar,
This 3rd day of Fegbruary, 2003.

Yosef Retta
President of Amhgara National
Region